# ትምክህት መረን የለቀቀ ኩራት

ኳሽኮርና ሪኬትስ የፕሮቲንና የቫይታሚን እጥረት የሚያመጣው የጤና መታወክ መሆኑን ድሮ ተምሬአለሁ። ጥጋብ የእብሪት መነሻ መሆኑንም የግብረገብ አስተማሪ አስረድተውኛል። ትምክህት ግን ከእውቀት ማነስ የሚመጣ በሽታ መሆኑን የነገረኝ አልነበረም። ምክንያቱም ለብዙዎቻችን ትምክህትና ኩራት ድብልቅልቃቸው ወጥቷል። ጀግንነትና ጨካኝነትም እንዲሁ። አሁን አውራሪስ ገዳይ፣ ዝሆን አዳኝና አንበሳ ገዳይ መሆን ምን ያኮራል? የገዛ ሰፈራቸው ደናቸው ድረስ ገብቶ አድፍጦ አውሬ ማደን ጨካኝነትና አላዋቂነት እንጂ እንዴት ጀግንነት ተብሎ ይፈረጃል? ለማንኛውም ጀግንነት ምን ማለት እንደሆነ ለሚያውቁት ልተወውና ትምክህት ከእውቀት ማነስ መምጣቱን ላውራ። ላውራ ማለቴ ያለምክንያት አይደለም።ይህ ጽሁፍ ሳይንሳዊ ጥናትና ምርምር ተደርጎበት የተጻፈ የሙያ ውጤት አይደለም። ግን ወደዚያው ሊያንደረድረን የሚችል ወቅታዊ ርዕስ ነው ብዬ አምናለሁ።

ኒኮላስ ቹቪን የሚባል ወታደር የነበረው ገደብ አልባ የአገር ፍቅርና (Inflated patriotism) ወሰን የለሽ የናፖልዮን ቦናፓርቴ ታማኝነት ምክንያት ትምክህት 'ቹቩኒዝም' የሚል ስም ወጥቶለት ጽንሰ ሀሳቡ በዐለም ናኘ። የታላቅነት፣ የእኔ እበልጣለሁ መረን የለቀቀና ድንበር የዘለለ ስሜትና አመለካከት ነው። በብዛት የሚጋሩት ሰዎች በአሉበት ጊዜ በወል ወደ ክብርና ኩራት የሚወሰድ ለሌሎች ግን ትምክት ተብሎ የሚፈረጅ አመለካከትን የመግለጫ ቃል መሆኑ ነው። እስቲ ትምክህትን ባጭሩ ሸንሸን አድርገን እንመልከት።

***የፆታ ትምክህት፡-*** መጋቢት ሲደርስ 'ትምክት' የምትለው ቃል ይመቻታል። መድረክ እስኪጠባት ድረስ። ይህም የዓለም አቀፉን የሴቶች ቀን የተመለከተ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የፆታ ትምክህትን ያስታውሰናል። ወንዶች ትምክህተኞች ስንሆን አላዋቂነታችንን አደባባይ ማውጣታችን ነው። አድሬናሊን በርከት ብሎ ሲረጭ የሚመጣ ጣጣ ይመስለኛል። በዚህ ጉዳይ ልመለስበት ብፈልግም የጾታ ትምክህትን ለወሬዬ መንደርደርያ ለማድረግ ነው ነው። ወንዶች፣ እኛ ወንዶች እንብርታችን ላይ በተገጠመልን እትብት ከእናታችን ጥሩ ጥሩውን እየመገመግን የሙጢኝ ካልንበት ማኅፀን በግድ በምጥ ስንወለድ እልል ሳይሆን እሪሪ ብለን አልቅሰናል። ምናምናችንን ጠራርጋ በእግር እስክንቆምና ነብስ እስክናውቅ የተንከባከበችንና ደምዋን፣ ወተትዋንና 26 ክሮሞዞሟን (ግማሽ ሴትነትዋን) የሰጠችን ወይም የምትሰጥን እናት ቁልቁል ካየናት የወንድ ትምክህት የአላዋቂነት ትልቁ ደረጃ መሆኑ ነው። በሀገ አራዊት እንኳ መጪውን ትውልድ ማለትም የእንበለዘር ጥበቃውን (species conservation) የምታዝበት ሴትዋ ናት። እንዲያው የእናትነት ፍቅር ሆኖባት እንጂ እየቆነጠጠች እያንቀጠቀጠች አሳድጋ ቢሆን እኮ እንኳን ሴት መናቅ ቀሚስ ስናይም በደነገጥን ነበር። ይህን የወንዶች ትምክህት ለመቋቋም ፈርጠም ያሉ ሴቶች ትንሽ እልፍ ቢሉና ሚዛን ቢደፉ ደግሞ የሴት ትምክህት መባሉ አይቀርም። በዚህ ልንደርደርና ሌሎች ዋና ዋናዋናዎቹንም ልነካካ።

**የሰው ልጅ ትምክህት፡-** የሰው ልጅ እራሱ የእግዜር ቃል ነው በሚል መጽሀፍ ቅዱስ ይዞ ዐለምን የምገዛ በራሱ በፈጣሪ አምሳል የተሰራሁ እኔ ብቻ ነኝ ሲል ትምክህት ነው። ግን በተቀረው፣ የሰው ልጅ እያጠፋ ባለው ሥፍር ቁጥር በሌለው ፍጥረት ዐይን ስለማናየው ትምክህት ልንለው አንደፍርም። ይህች ዐለም ግን ለሁሉም ፍጡር የጋራ መሆንዋን የአንዳቸው መጓደል አጠቃላይ ቀውስ ሊያመጣ እንዲሚችል ባለማወቃችን አንጨነቅበትም። ይህን ዐለምን በመዳፍ የማስገባት የሰው ልጅ ትምክህት (Human or species chauvinism) እንበለው? ነገር ግን ከፍጡራን ሁሉ ይህንኑ ዐለም ለማጥፋት እየተስገበገበ ያለው ዓለምን ከእግዜር በሊዝ ተቀብያለሁ የሚለው የሰው ልጅ ለመሆኑ መረጃ ማጣቀስ እንኳ አያሻም። እንኳን ሌላውን የራሱን ዘር እንኳ ለማጥፋት በቂ ምክንያት የማይሻ የሰው ልጅ ብቻ ነው። ለከባቢው አየር መዛባት፣ ለደን መመንጠር፣ ለእንበለዘር ጥፋት ሁሉ ዋንኛ ተጠያቂ እኛው አይደለን?

**አገራዊ ትምክህት፡-** ጀርመን የተለየች አገር መሆንዋን በውስጣቸው የሚፈሰው ደም ከሌላው ሁሉ መላቁን ከፍ አድርጋ በመስበኳ አገራዊው ትምክህት ፋሺዝምን ወለደ። አንዱን አሳርሮ አንዱን በሊጥ አውጥቶ በስተመጨረሻ እኛን ሰራ ብለን ስንቀልድም የአገራዊ ትምክህት ነው። ለዚያውም ያረሩ ከሚባሉት የሚመደቡትን የኛኑ ወገኖች እንደ ኢትዮጵያዊ ያለማየት አደጋ ያለው ትምክህት ይሆናል። እኛ ፊት ሲቀለድ ያስቀናል አንዳንዶቻችንን ያኮራናል።ይቺ ምን አላት ልንል እንችል ይሆናል። ነገር ግን ብዙ የጎረቤት ግጭቶችንም ሆኑ የጎጥ ንቅናቄዎችን የዚች አይነትዋ ትምክህት ነች ጉልበት የምትሰጥ። ኢትዮጵያ ከሌሎች ሁሉ የተለየች እንደሆነችና ሌሎች በአፍሪካ ያሉትን ጎረቤቶቻችንን አሳንሰንና ንቀን ስንመለከት አገራዊ ትምክህት ይሆናል። ይሄ የሚያማቸው ብዙ የአፍሪካ ወንድምና እህቶች እንዳሉን የገጠመን ያየነው እናውቀዋለን። ይህ ነገሮችን በውል ባለማወቅ አንድነትና ልዩነትን በመብለጥና በማነስ ብቻ የመፈረጅ ስህተት ይመስለኛል። ቀዳዳ ቁምጣ እየለበስን ያሸረጠውን ሸርጣም ስንል ትምክህት ነው። ለዚያውም የሚያሸርጡ ያገር ልጆችም እያሉ ማለት ነው። ይህ ያለማወቅ ጥርስ ያናክሳል። እንጀራ የምንበላ እግረ ቀጫጭን አበሾች የበቆሎ ገንፎ የሚበሉትን ጠብደል ኬንያኖች ስንንቅ ከምቾት ቀጠናችን ቆመን ነው። እነርሱም ሊሉን የሚችሉት እንደሚኖር ግን ብዙም ልብ አንልም።ከምስራቅ እስከ ምዕራብና ደቡብ አፍሪካ ድረስ ብትዘልቁ መነሻችን ኢትዮጵያ ናት የሚሉ በልባቸው ኢትዮጵያን ከፍ የሚያደርጉ ብዙ ሕዝቦች የኛን ትምክህት ቢሰሙ ምንኛ በጠሉን። ይህ ታድያ ለሁላችን የሚሰጥ መለያ አይደለምና አትዘኑብኝ። ነገር ግን እንዲህ የምናስብ ደግሞ መኖራችንን መካድ ሌላ ትምክህት ይሆናል። የሌሎችን ሳንንቅ ያለንን ማክበር፣ ማሳደግና ማስፋፋት ግን ብልህነት እንጂ ትምክህት አይደለም።

**የጎጥ ትምክህት፡-** የዘር፣ የጎጥ፣ የጎሳ ትምክት ሌላው ነው። አንዱ ሌላኛውን የሚያጣጥለው ስለሌላው የሚያውቀው በጣም ትንሽ ስለሆነ ነው። ቆለኛው ደገኛውን ይንቀዋል። ቆለኛው እንደ ደገኛው ቢያስብ በብልኮ ተጀቡኖ መሄዱ ብርድ ለመከላከል መሆኑን ይረዳል። ገብስ መብላቱም ጥቅም እንዳለው ይገነዘባል። በተመሳሳይ ቆለኛው ቁምጣ መልበሱ እራቁትን መሄዱ ሳይሆን ሙቀቱን መከላከሉ መሆንን ያውቀለት በነበር። ዘንጋዳ መብላቱም ጉዳት እንደሌለው መረዳት በቻለ። ይህ ድንቅ የሰው ልጅ አካባቢን መስሎ የመኖር ችሎታ የሚያኮራ እንጂ የሚያናንቅ ያለመሆኑን ባለማወቅ ነው አንዱ ሌላኛውን የሚተቸው። ታደሰ የሚለውን ታዳሳ ብሎ ስለጠራ የሚስቀው አማርኛ ተናጋሪ በኦሮምኛ ደከመኝ ለማለት 'ደ' ን እያጠበቀ 'ደደቤ' ብሎ ቢናገር ከት ብለው እንደሚስቁበት አያውቀውምና ተስቆበት እስኪናደድ ስቆ ይመጻደቃል። አንዱ ለኦሮሞ ነጻነት ለመታገል ጠመንጃ የያዘ ሰው ስለአማራ ትምክት ብዙ አስረድቶኝ የቆመበትን የእውቀት ኬላ አሳየኝ። አብረን ስናወራ ቆየንና በጨዋታ መሀል «ያው

እንደምታውቀው ምንና ቆርቆሮ ሳይነኩት ይጮኻል» ብሎኝ አረፈው። ከቀልዱ ይልቅ የሚታገለው የትምክህት ዛር እርሱም ላይ ሰፍሮ በማየቴ ከት ብዬ ሳቅሁ። በሁዋላ ያንተን የምን ትምክህት ልበለው? እነርሱም ጠመንጃ ያንሱና አንተን ይታገሉህ ወይ? ብዬ ስለትምክህት ለማስተማር መግቢያ ቀዳዳ አገኘሁለት። ብናውቅበት ከምንናናቅ ተያይዘን ባደግን ነበር። እርግጥ ነው አስተዋዮች ሆነን ወይም እንጀራ አቀራርቦን ተቀላቅለን ስንኖር ከመንደራችን ሳለን የነበረን ግምት ሁሉ ከንቱ መሆኑን ማወቅ እንገደዳለን። ጭራሽ ፍቅር አሸንፎን ተጋብተንና ተዋልደን እናርፈዋለን።

**የሙያ ትምክህት፡-** አንዳንዶች ደግሞ የነርሱ ሙያ ከሌላው ሁሉ የላቀ፣ ወደር የማይገኝለትና ሌላው የዚህ ሁሉ ተቀጥላ ወይም ተሳቢ እንደሆነ አድርገው ይመለከታሉ። ያ ደግሞ የሙያ ትምክህት ይሆናል። ተደጋጋፊ፣ ተያያዥና አስፈላጊ የስራ ክፍፍል እንደሆነ አድርገው አይመለከቱም። ሙያን ማፍቀር ተገቢ ሆኖ ሳለ ሌላውን አሳንሶ ማየት ግን ሙያዊ ትምክህት ይሆናል። ትምክህት የማንንም ደጅ ትረግጣለች። ዲግሪና ዲፕሎማም አያግዳትም። አንዳንድ ምሁራን ከነርሱ ሙያ ሌላ ትልቅ ነገር ያለ አይመስላቸውም። በተለይ ስማቸው ላይ ቅጽል ከገባበት አየር እንደተሞላ ፊኛ ከሰው አናት መዋል የሚሹ አሉ። መምህራን A ን ለእግዚአብሄር፣ B ን ለእኔ ሲሆን ከ C ጀምሮ ለተማሪ ብለው ሲመጻደቁ ትምክህት ነው። ምክንያቱም ተመጥኖ የሚሰጣቸውን ትምህርት ጠንቅቀው ካወቁ ለደረጃው የሚገባው ውጤት ለተማሪዎች ሊሰጣቸው ይገባልና። መምህር በልጦት የሚሄድ ተማሪን ሲያፈራ እድገት ይኖራል። ከእርሱ ያነሱ ወይም የሚያንሱ ተማሪዎችን ማፍራት ግን ትውልድ ማቀጨጭ ይሆናል። ተማሪ አስተማሪው ካቆመበት ልጅ ወላጆቹ ካቆሙበት እያሻሻለና እያጎለበተ ካልሰራ እድገት የሁዋልዮሽ ይሆናል። ስለዚህ ሙያዊ ትምክህትም አደገኛ ነው። አገራችን ውስጥ አንዱ ሌላው ባጎደለው ከመደጎም ይልቅ ማንጓጠጥና ያላወቀውን አገዝፎ ማውጣትና መውገር ብርታት የሚሰጣቸው ወገኖች አሉ። እኔ የማውቀው እንዲህ ነው ከሚሉ እነርሱ ምንም አያውቁም ሲሉ የሚቀላቸውን ለማለት ነው።

**የፖለቲካ ትምክህት፡-** ይሄ እንኳ ለሁላችንም ግልጽ ነው። እኛ ብቻ ነን አዋቂዎች፣ እኛ በከፈልነው መስዋዕትነት ሌላው አይደሰትም የሚሉ ፖለቲካውን እንደ እርስት የያዙ ድርጅቶችና መሪዎች ለሌላው ስፍራ አልሰጥ ሲሉ፣ ሲንቁና ሲያጣጥሉ የፖለቲካ ትምክህት ይሆናል። በሚያራምዱት የፖለቲካ አስተሳሰብና በቀረጹት ፕሮግራም እንድንከተላቸው ሳይሆን ለራሳቸው በቀረጹት ታቦት እንድንሰገድላቸው ሲሹ ማለት ነው።

**የሀይማኖት ትምክህት፡-** ሐይማኖት ነብስን ከፈጣሪ ጋር የማገናኛ ስጋንም የመግሪያ መንገድ ነው። እንደ አማኙና ቀኖናው የተለያየ፣ ነገር ግን ሁሉም መልካም ማድረግን የሚያስተምሩ ናቸው። ነገር ግን የኔው ከሌላው ይልቃል አይነት መኮፈስ የሀይማኖት ትምክህት ይሆናል። በዚህ ምክንያት የተነሱ ጦርነቶች ጥቂት አልነበሩም። ተመሳሳይ ቀኖና ያላቸው እንኳ በአንድ እግዚአብሄር የሚያምኑ ተመሳሳይ ገነት ስለመኖሩ የሚቀበሉ ግን የኛው አቋራጭ ነው በማለት የሌላውን መንገድ የሚንቁና የሚያጣጥሉ የሀይማኖት ትምክህተኞች ይባላሉ። ይህ ግን ሀይማኖትን ለፖለቲካ ወይም አገራዊ ጥቅም ከሚገለገሉበት ለየት ይላል።

**የቤተሰብ ትምክህት፡-** የኛ ዘመዶች የሚል ትምክህትም አለ። የኛ ዘመዶች እኮ እነ ሞት አይፈሬ፣ ባለጠጎች፣ አዋቂዎች.... የሚል ትምክህትም አለ። ሰብሰብ ብለው የሚሞካሹበት ሌላውን የሚያንኳጥጡበት። የአያ እገሌ የአቦ ማንትስ ልጆች የልጅ ልጆች እየተባለ ደረት የሚነፋበት ማለት ነው። መቸም አልፎ አልፎ ሳያጋጥማችሁ አይቀርም። ይህ የኛ ብቻ ሳይሆን ማኅበራዊ ኅይወት ያለበት የትኛውም የዐለም ክፍል የአለ ነው። የኛ እንኳ አሁን ችምችም ያለ ቤተዘመድ ስደትና ሰፈራ አሳስቶታል። ግን እንደዚያ ያለ ትምክህትም አለ ብሎ ለመጠቆም ነው፡ ይህን የቤተሰብ (ቤተዘመድ) ትምክህት ልንለው እንችላለን።

ስለዚህ ደረጃ በደረጃ ከወረድን ቤተሰብና ግለሰብ ድረስ የሚወርድ የሰው ልጅ ባለማወቁ፣ ባለመረዳቱ፣ ከገደብ በላይ አገሩን፣ ጎሳውን፣ ቤተሰቡን ወይም ራሱን ከፍ በማድረጉ ምክንያት ሚዛናዊነቱን ሲስት የሚከስት ኩራት ነው ወደ ትምክህትነት የሚለወጠው። እናም በመከባበር እንጂ በመናናቅ ሰላም አይኖርምና እንደ ፍጡር፣ እንደ ዜጋ፣ እንደ ቤተሰብም ይሁን እንደ ፆታችን አእምሮን፣ ነፍስንና ስጋን በጋራ በማሰራት ለእግዜርም ለፍቅርም መገዛት ተገቢ ነው። ለአለንበትና ለመጪውም የሚበጀንን ለማድረግ ትምክህትን በትምህርትና በእውቀት ብንለውጠው ለኳሽኮርና ሪኬትስ መድሀኒት እንዳገኘነው ሁሉ ለትምክህትም መፍትሄ ማግኘት ያስችለናል ብዬ ወሬዬን አጠር ላድርገው። አዘውትረን በክስና በእርግማን ጊዜ እንዳናጠፋ መሰረታዊ የሆነ እውቀት የሚያስጨብጡ ጉዳዮችን ቀለል በአለ አቀራረብ ሊያስተምሩን የሚችሉ ምሁራን መንገድ ስንስት ከሚተቹን አውቀን እንድንጓዝ ቢደግፉን ካሰብንበት ፈጥነን እንድንደርስ ይረዳናል።

ፍቅር ይስጠን፣ መቻቻልን ያብዛልን!!

ዳኛቸው ቢያድግልኝ
biyadegelgne@hotmail.com